ሚያዝያ 25 ቀን 2004 ዓ.ም

የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የ2003 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት በተመለከተ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ የፌዴራል ዋና ኦዲተር ሪፖርት

የተከበሩ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ ም/አፈ ጉባዔና

የተከበራችሁ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢ.ፌዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 101/2 እና መሥሪያ ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 669/2002 አንቀጽ 5 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 18 እንዲሁም በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተሰጠው ስልጣን መሠረት መ/ቤቱ ኦዲት ያደረገውንና ያስደረጋቸውን የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የኦዲት ሪፖርት፣ የፌዴራል መንግሥት ለክልል መንግሥታት በመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ (Protection of Basic Services) ፕሮግራም የሰጠውን የበጀት ድጋፍና ድጎማዎች ተከታታይ ኦዲት የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርቶች፤ የመንግሥት መ/ቤቶች አሠራር ህጉን የተከተለ፣ ያስገኙት ውጤት ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ እና ተፈላጊውን ግብ የመታ መሆኑን ለማረጋገጥ የተደረገውን የክዋኔ ኦዲት፣ እንዲሁም ስለመ/ቤቱ አጠቃላይ ሥራዎች ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ዓመታዊ ሪፖርት እንደሚያቀርብ የተደነገገ በመሆኑ፣ በዚሁ መሠረት በ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የተከናወኑ ኦዲቶች ሪፖርትና የ2003/2004 ኦዲት ዓመት ዕቅድ ክንውን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱት፤

1. በልዩ ልዩ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሂሳብ ላይ የተከናወኑ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት፣ የክዋኔ ኦዲት እና በመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ፕሮግራም ለክልሎች የተሰጠ ድጋፍ (Protection of Basic Services) ተከታታይ ኦዲት የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርቶች ናቸው።

2. ሪፖርቱ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና የሙያ ፈቃድ በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት የተደረጉትን በውጭ እርዳታና ብድር የሚካሄዱ ፕሮጄክቶች/ፕሮግራሞችና የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ሂሳብ ኦዲት ያካትታል።

3. በዚህ ሪፖርት ውስጥ የሚቀርቡ የ2003 በጀት ዓመት የተለያዩ የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ሂሣብ የኦዲት ዕቅድና ክንውን እና ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች፣ የመሥሪያ ቤቱን አጠቃላይ የሥራ ይዞታ፣ በኦዲት ሥራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች እና የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴን ያጠቃለለ ነው።

4. የ2003 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲትን በተመለከተ በመ/ቤታችን የተከናወኑ ዝርዝር የኦዲት ሪፖርቶች ራሳቸውን ችለው በተጠናቀሩ 2 ጥራዞች ለም/ቤቱ የቀረቡ ሲሆን እነዚህን ሪፖርቶች የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም የሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች በሚገባ በመመርመር አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ እንዲያስችል በጥልቀት ተዘጋጅቷል፡፡ የሪፖርቶቹም ቅጅ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት እንዲደርስ ተደርጓል።

5. እያንዳንዱ የኦዲት ሥራ እንደተፈጸመ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ኃላፊዎች ጋር በኦዲቱ ግኝቶች ላይ የመውጫ ውይይት (Exit conference) ከመደረጉም ሌላ የኦዲት ሪፖርቱ ተልኮላቸው መ/ቤቶቹ ለሥራ አመራር ሪፖርቱ የሰጡትን ምላሽ ያገናዘበ በመሆኑ የመረጃዎቹ ተአማኒነትና አግባብነት በሁሉም ወገን ተቀባይነት እንዳለው ይታመናል።

6. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት የዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት፣ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብት፣ ሰነዶች፣ የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ሲሆኑ፣ ኦዲቱም የተከናወነው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፣ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነትና አግባብነት ሙሉ በሙሉ ኦዲት በማድረግ ነው።

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የ2003 በጀት ዓመት ሂሣብ

ኦዲት ዕቅድና ክንውን

የፋይናንስና ሕጋዊኒት ኦዲትን በተመለከተ

7. በ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ አቅራቢ ከነበሩት 164 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች መካከል በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን ኦዲት እንደሚደረጉ ታሳቢ የተደረጉትን 20 መ/ቤቶች ጨምሮ በ150 መ/ቤቶች የኦዲት ሥራ ለማከናወን መታቀዱ ይታወሳል፡፡ በመ/ቤታችን በኩል ኦዲት ለማድረግ በታቀዱት 130 መ/ቤቶች ላይ 1 በመጨመር የ131 መ/ቤቶች ወይም የታቀደው ኦዲት 100% የተከናወነ ሲሆን፣ በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን በኩል ኦዲት ለማድረግ የታሰቡት 20 በድምሩ የ151 የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ኦዲት በመከናወኑ የኦዲት ሽፋኑን 92.07% ለማድረስ ተችሏል፡

8. የተሰጠውም የኦዲት አስተያየት ዓይነት ሲተነተን፣ ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት 57፣ ነቀፌታ ያለበት አስተያየት 52፣ አቋም የማይወሰድበት አስተያየት 7፣ ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የቀረበበት 13 እና ሂሰባቸውን በወቅቱ ያልዘጉ 2 በድምሩ 131 ናቸው፡፡

በፌዴራል መንግሥት የልዩ ልዩ መ/ቤቶች የፋይናንስና

ሕጋዊነት ኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች

9. መ/ቤታችን ምክር ቤቱ ያጸደቀው በጀት የፋይናንስ አስተዳደር ሕጉን፣ ደንብና መመሪያ በሚፈቅደው መሠረት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ በ2003 በጀት ዓመት የልዩ ልዩ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ሂሳብ ላይ ባከናወነው ኦዲት በርካታ የሂሣብ አያያዝ ግድፈቶች እና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እንዲሁም አፈጻጸማቸው ከደንብና መመሪያ ውጭ የሆኑ ሁኔታዎች ተገኙ ሲሆን የም/ቤቱን ትኩረት ሊያገኙ ይገባል ተብሎ የታመነባቸው አንኳር አንኳር ግኝቶች ብቻ ተለይተው እንደሚከተለው ቀርቧል ::

የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

10. የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ትክክለኛነት አያያዝና አጠባበቅ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ4 መ/ቤቶች ብር 1,066,524.68 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡

11. የጥሬ ገንዘብ ጉድለቱ የታየው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብና በሂሳብ መዛግብትና የሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ጋር በውስጥ ኦዲተሮች ሲመዛዘን መሆኑ ታውቋል፡፡

12. በመሆኑም በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲተካ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

<u>ውዝፍ ተሰባሳቢ ሂሣብ</u>

13. በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እስከ 35 በተደነገገው መሠረት የተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ መወራረዱ ሲጣራ በ59 መ/ቤቶች ብር 1.27 ቢሊዮን የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሠረት በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡

14. ከዚህ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት የትምህርት ሚኒስቴር ብር 723.77 ሚሊዮን፣ የመከላከያ ሚ/ር ብር 133.78 ሚሊዮን፣ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ብር 115.02 ሚሊዮን፣ ጤና ጥበቃ ሚ/ር ብር 48.05 ሚሊዮን፣ በግብርና ሚ/ር 38.55 ሚሊዮን፣ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫና ፈተናዎች ኤጀንሲ ብር 35.16 ሚሊዮን፣ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ብር 31.79 ሚሊዮን፣ ውጭ መልዕክተኞች 29.97 ሚሊዮንና በፌዴራል ፖሊስ 23.99 ሚሊዮን ይገኙበታል፡፡

15. በመሆኑም በቅድሚያ ክፍያ የተሰጡት ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ፣ ማስረጃ ያልቀረበላቸውም ሂሳቡ ተጣርቶ አስፈላጊው ማስረጃ እንዲቀርብና ማስተካከያ እንዲደራግለቸው፣ በተሰበሳብ ሂሳቦች ላይ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

<u>የገቢ ሂሣብ</u>

16. የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

<u>በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት</u>

<u>ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሣብ</u>

17. የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ16 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 952.94 ሚሊዮን በተለያዩ ምክንያቶች ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡

18. በአዋጁ መሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች፤ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 638.14 ሚሊዮን፤ ምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ብር 132.56 ሚሊዮን፤ ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 10.58 ሚሊዮን፤ እና የውሃና ኢነርጂ ሚ/ር ብር 120.63 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

19. ስለሆነም መ/ቤቶቹ የመንግሥት ገቢ ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት ገቢዎችን መሰብሰብ እንዳለባቸው፣ በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ

20. ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ህግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በወቅቱና በአግባቡ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤትና በስሩ ባሉ ሰባት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከውዝፍ ግብር፤ ወለድ እና ቅጣት መሰብሰብ የሚገባው ብር 272.15 ሚሊዮን እና በሌሎች 4 መ/ቤቶች ብር 1.62 ሚሊዮን በድምሩ ብር 286.77 ሚሊዮን በወቅቱ ያልተሰበሰበ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

21. ይሁንና ገቢን በወቅቱ መሰብሰብ መንግሥት ለሚያከናውነው የልማትና ማህበራዊ ሥራዎች ወሳኝ በመሆኑ አሁንም ለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶት የመንግሥት ገንዘብ በወቅቱ እንዲሰበሰብ እናሳስበለን፡፡

በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ ገቢ

22. በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ 18 መ/ቤቶች የሰበሰቡትን የውስጥ ገቢ ብር 138.59 ሚሊዮን ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ አለማካተታቸው፤ እንደዚሁም በ9 መ/ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 10/2 መሰረት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርን ሳያስፈቅዱ የጥሬ ገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ በስማቸው በማሳተም ከልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ምንጮች ገንዘብ የሚሰበስቡና ሪፖርትም የማያደርጉ ተገኝቷል፡፡ የገቢ ሂሳብ በሪፖርት የማያካትቱት በአብዛኛው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መሆናቸው ታውቋል፡፡

23. ይህ አሰራር በመ/ቤቶች የሚዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎችና የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪም ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ የሚያደርግ በመሆኑ መ/ቤቶች የሚሰበስቡትን ማንኛውም የመንግስት ገቢ ሕጋዊ በሆነ መንገድ በታተሙ ደረሰኞች ብቻ በመጠቀም

እንዲሰበስቡና በሂሳብ መግለጫዎችም በመካተት ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

<u>በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ</u>

<u>የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች</u>

24. የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢ የሆኑ የቁጥጥር ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል::

- በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ስር ባሉ ሶስት ቅ/ጽ/ቤቶች እና በሌሎች ሶስት መ/ቤቶች በድምሩ ብር 225.58 ሚሊዮን የገቢ ደረሰኝ፤ የግብር ማሣወቂያና ሌሎች መረጃዎች በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ ምክንያት፤ ከማን እንደተሰበሰበ ሳይገለጽ በኮድ በመሰብሰቡ የተሰበሰበው ገቢ መሰብሰብ በሚገባው ልክ መሆኑን ለማረጋገጥ አለመቻሉ፤

- በቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚዎች በአዋጅ ቁጥር 543/1999 አንቀፅ 11(7) መሰረት ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ አራት ድርጅቶች ጥሬ ዕቃ ያስገቡ እና ጥሬ እቃው ስራ ላይ ውሎ ምርቱን ወደ ውጭ መላክ ያለባቸው ቢሆንም፣ ምርቱ ሳይላክ ከአንድ አመት በላይ የቆየና የፈቃድ ማራዘሚያም ያልተደረገ መሆኑ፤

- የገቢ ደረሰኞች ከዋና መ/ቤት ወደ ቅርንጫፍ መ/ቤቶች ወይም ጽ/ቤቶች ሲላኩ በተቀባዩ የንብረት ገቢ ደረሰኝ የማይቆረጥላቸውና በተሰበሰበውም ገቢ ላይ ተገቢው ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፤

- የፌደራል ስፖርት ኮሚሽን በስታዲዮም ዙሪያ ከሚያከራያቸው የንግድ ቤቶች የሚሰበስበው የኪራይ ገቢ ከ15 ዓመታት በፊት በተተመነ ዋጋ መሰረት መሆኑ፤

- የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች ከሆኑት ሠራተኞች ሊሰበሰብ የሚገባውን ገቢ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፤ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት፤ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም፤ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የማይሰበስቡ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

25. ስለሆነም ለወደፊቱ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሠራ፤ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት የገቢ አሰባሰብ እና የአሠራር ድክመቶች እንዲታረሙና ባጠቃላይ የገቢ አሰባሰቡ የገቢ

አዋጅ፣ ደንቡንና መመሪያውን ተከትሎ መፈፀም እንዳለበት በሰጠነው አስተያየት መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

<u>የወጪ ሂሣብ</u>

26. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች መሠረት በአግባቡ መጠቀማቸውን፣ ተገቢው ማስረጃ መቅረቡንና ሂሳቡም በትክክል መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

<u>የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሣብ</u>

27. በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ12 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 38.66 ሚሊዮን፤ በሌሎች 22 መ/ቤቶች ደግሞ ምንም ማስረጃ ሣይኖረው ብር 79.52 ሚሊዮን በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

    ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ፤ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚያሣይ ዝርዝር መረጃ ሳይደገፍ፤ በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን የሚገልጽ የወጪ ማስረጃ ሣይቀር በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ጎላ ያሉት ናቸው፡፡ የተሟላ ማስረጃ ካለቀረቡት መ/ቤቶች መካከል መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 23.34 ሚሊዮን፤ ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ብር 6.77 ሚሊዮን፤ አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 2.89 ሚሊዮን፤ ጎንደር የኒቨርሲቲ ብር 2.49 ሚሊዮን ሲሆን፤ ማስረጃ ሳይቀርብ ወጪ ካደረጉት ውስጥ ደግሞ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ዋናው መ/ቤት ብር 19.36 ሚሊዮን፤ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ብር 14.41 ሚሊዮን፤ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 6.89 ሚሊዮን፤ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 6.21 ሚሊዮን፤ ገቢዎችና ጉምሩክ ብር 3.89 ሚሊዮን፤ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 3.44 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

28. ማንኛውም ሂሳብ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ፣ ደንቡና መመሪያ መሠረት ማስረጃዎች መሟላታቸው እንዲረጋገጥ፣ ያልተሟሉት ማስረጃዎች እንዲሟሉና ለወደፊቱም ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ አሳስበናል፡፡

<u>ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈጸሙ ግዢዎች</u>

29. የዕቃና አገልግሎት ግዢ በደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ33 መ/ቤቶች ብር 313.26 ሚሊዮን የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል።

30. ከደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 224.22 ሚሊዮን፤ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 41.38 ሚሊዮን፤ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ብር 7.56 ሚሊዮንና የመቀሌ ጤና ሳይንስና አይደር ሪፈራል ሆስፒታል ብር 3.06 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

31. ካልተከተሏቸው የግዥ ደንብና መመሪያዎች ውስጥ የጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ያለጨረታ ማስታወቂያ በመግዛት፣ በዋጋ ማወዳደሪያ /ፕሮፎርማ/ አማካኝነት መፈጸም ያለበትን ግዥ ውድድር ሳይደረግ በመፈጸም፤ ተገቢ የውል ስምምነት ሳይደረግ እና በአቅራቢነት ካልተመዘገቡ ድርጅቶች ግዥ ማከናወን የሚሉት ይገኙበታል፡፡

32. የግዢ መመሪያን ሳይከተሉ ግዢ መፈጸም ለምዝበራ፣ ለጥፋትና ጉድለት የሚዳርግ በመሆኑ የመንግሥት ግዢ ደንብና መመሪያን አክብረው በማይሠሩ መ/ቤቶች ላይ የተጠናከረ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

<u>ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች</u>

33. ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች ደንብና መመሪያ ተጠብቆ ክፍያ መፈጸሙ ሲጣራ በ26 መ/ቤቶች ብር 237.16 ሚሊዮን ከደንብና መመሪያ ውጭ ተከፍሎ ተገኝቷል።

34. ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ከተፈጸሙ ክፍያዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ፤ በጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 119.53 ሚሊዮን፤ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 79.29 ሚሊዮንና ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 34.52 ሚሊዮን ሲሆን፤ ምክንያቶቹም የምህንድስና ክፍል የቁጥጥርና የማማከር ፈቃድ ሳይኖረው የተከፈለ፤ ለማበረታቻና ለሽልማት በቦርድ ሳይጸድቅ የተከፈለ፤ በግንባታ ቦታ ላይ ያሉ ዕቃዎች (materials on site) ተብሎ የተከፈለና ሌሎችም የትርፍ ሰዓት ክፍያ በመፈጸም፤ ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎ አበል በመክፈልና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወጪ የተደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

35. በመሆኑም ከደንብና መመሪያ ውጪ ያለአግባብ የተከፈለው ሂሳብ ተመላሽ እንዲሆንና ለወደፊቱም ደንብና መመሪያዎች ተከብረው መሰራት እንዳለበት ኦዲት ለተደረጉት መ/ቤቶች አሳስበናል፡፡

<u>አላግባብ በወጪ የተመዘገበ ቅድሚያ ክፍያ</u>

36. በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ8 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች የተከፈለ ቅድሚያ ክፍያ ብር 981.86 ሚሊዮን በወጪ የተመዘገቦ ተገኝቷል፡፡

ቅድሚያ ክፍያን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል ትምህርት ሚ/ር ብር 539.69 ሚሊዮን፤ ጂማ ዩንቨርሲቲ ብር 168.43 ሚሊዮን፤ ውሃና ኢነርጂ ሚ/ር ብር 155.84 ሚሊዮን እና አርባ ምንጭ ዩንቨርሲቲ ብር 68.16 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

37. በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፤ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብበት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት</u>

38. የመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ የተገዛው ንብረት ለመ/ቤቱ ገቢ ለመሆኑ የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ9 መ/ቤቶች በብር 83.99 ሚሊዮን የተገዙ ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

39. ከዚህም ውስጥ ትምህርት ሚ/ር ብር 75.26 ሚሊዮን፤ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 4.02 ሚሊዮን እና የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ብር 3.9 ሚሊዮን የተገዛው ዕቃና ንብረት ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

40. የዚህ ዓይነት አሠራር የመንግሥት ንብረትና ሀብትን ለምዝበራና ብክነት ስለሚያጋልጥ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ጥንቃቄ ሊደረግና የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበላቸው ንብረቶች ለየመ/ቤቶቹ አገልግሎት ለመዋላቸው በማስረጃ እንዲረጋገጥ ለመ/ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ

41. በበጀት ዓመቱ መ/ቤቶች የፈጸሙት ክፍያ ትክክለኛነት ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ8 መ/ቤቶች ብር 2.03 ቢሊዮን በተለያየ ምክንያት የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡

42. የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለው ሂሣብ ውስጥ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ለሠራዊት ደመወዝ ወጪ ያደረገው ብር 1.87 ቢሊዮን፤ ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ብር 54.25 ሚሊዮን፤ እንዲሁም የውስጥ ደህንነት ጥበቃ ዋና መምሪያ ብር 33.34 ሚሊዮን እና የኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ ብር 49.99 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

43. የሶስቱ የደህንነት መ/ቤቶች ለደመወዝ ለነዳጅና ለስልክ ወዘተ... ወጪ ያደረጉት ሂሣብ ለማረጋገጥ ዝርዝር መረጃዎች እንዲቀርቡ ተጠይቆ ባለመቅረቡ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ የሀገር መከላከያ ሚ/ር በላከው መልስ ከመረጃው ሚስጥራዊነትና ከደህንነት አንጻር ችግር ያለበት በመሆኑ፣ ለወደፊቱም ቢሆን እንደዚህ አይነት ዝርዝር ከሚስጥርና ደህንነት ጋር የተያየዙ ሰነዶችን አሳልፎ መስጠት አስቸጋሪ መሆኑ ተገልጿል፡፡

በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ

44. የውስጥ ገቢ እንዲሰበስቡና እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢያቸው ያወጡትን ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያቀርቡት የሂሳብ ሪፖርት የሚያሳውቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ8 መ/ቤቶች ብር 55.27 ሚሊዮን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ የወጪ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡

45. አሰራሩ የየመ/ቤቶቹ የፋይናንስ አፈጻጸምና የፌዴራል መንግስት አመታዊ አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ ትክክለኛ ገጽታ እንዳይኖራው ስለሚያደርግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገውና በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የውስጥ ገቢም ሆነ ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የተከፋይ ሂሣብ

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ

46. በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ36 መ/ቤቶች ብር 247.97 ሚሊዮን በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

47. በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች ሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 144.43 ሚሊዮን፣ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ብር 49.58 ሚሊዮን፣ ውጭ መልዕክተኞች ብር 19.33 ሚሊዮን፣ አዲስ አበባ ንግድ ስራ ት/ቤት ብር 9.68 ሚሊዮን፣ በወሎ ዩኒቨርሲቲ ብር 5.03 ሚሊዮን፣ አርዳይታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ብር 3.85 እና ጤና ጥበቃ ሚ/ር ብር 3.15 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

48. የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በሰኔ 30/2003 ከሠራዊት ደመወዝ ተመላሽ ተብሎ ሪፖርት የተደረገው ብር 144.43 ሚሊዮን የተወሰኑ የሠራዊቱ አባላት ደመወዝ ባለመውሰዳቸው ለረጅም ዓመታት በተከፋይ ሂሣብ የተያዘና ሂሣቡም በወጪ በመመዝገቡ፣ አሠራሩ ከመንግሥት የሂሣብ አሠራር ውጭ በመሆኑ እንደማንኛውም የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት ያልተከፈለ ደመወዝ በቀጣዩ ወር መጀመሪያ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ መደረግ እንዳለበት፣ ደመወዝ ካልተከፈላቸው አባላት ጥያቄ ሲቀርብ ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር እየተጠየቀ እንዲከፈልና ሌሎችም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው እንዲከፍሉ አሳስበናል፡፡

49. በተጨማሪም ያለበቂ ማስረጃ በተከፋይ ሂሳብ የተመዘገቡ፣ ዝርዝር ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥ ያልተቻለ፣ በተከፋይ ሂሳብ መግለጫ ያልተካተቱ፣ እንዲሁም ያልተለመደ የሂሳብ ሚዛን የሚያሳዩ ተከፋይ ሂሳቦች በተለያዩ ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች ተገኝተው አስፈላጊው ማስረጃ እንዲቀርብና ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግላቸው ለየመ/ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የበጀት አጠቃቀም

50. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በአግባቡ መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ በተደረገው ኦዲት በ29 መ/ቤቶች ከተደለደለው በጀት በላይ በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ሥራ ላይ ያዋሉ ብር 288.58 ሚሊዮን፣ እንደዚሁም በሌሎች 92 መ/ቤቶች ደግሞ በጀቱ ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ተደልድሎ ያልተሰራበት ብር 3.05 ቢሊዮን ተገኝቷል።

51. ከበጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 102.40 ሚሊዮን፤ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ብር 67.40 ሚሊዮን፤ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 47.44 ሚሊዮን፤ ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 24.07 ሚሊዮን እና ጥቁር አንበሳ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 20.82 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ በጀቱ ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ተደልድሎ ካልተጠቀሙበት መ/ቤቶች መካከል የትምህርት ሚኒስቴር ብር 898.94 ሚሊዮን፣ ውሃና ኢነርጂ ሚ/ር ብር 718.99 ሚሊዮን፣ የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 248.46 ሚሊዮን፣ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 193.23፣ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 148.39 ሚሊዮንና የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ብር 133.79 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

52. በመሆኑም መ/ቤቶች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት የተፈቀደላቸውን በጀት በተገቢው መንገድ የበጀት ዝውውር በማድረግ አስፈቅደው ሥራ ላይ ማዋል እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

የንብረት አስተዳደር

53. መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም፤ በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው የዕቃና ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ፡-

ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	26 መ/ቤቶች
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	15 መ/ቤቶች
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	22 መ/ቤቶች
የቋሚ ዕቃ መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም ምዝገባ ያላከናወኑ	22 መ/ቤቶች
አገልግሎት ላይ ያልዋሉ ንብረቶች የተገኙባቸው	8 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	33 መ/ቤቶች
ተያያዥነት ያለቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	7 መ/ቤቶች

መሆናቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

54. በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥትን ንብረት ለምዝበራና ብክነት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ምዝገባና ቁጥጥር እንዲያከናውኑ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>በንብረት አያያዝና አስተዳደር ረገድ የታዩ</u>

<u>የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች</u>

- በአንዳንድ መ/ቤቶች ግዥ በተደጋጋሚ ያለዕቅድ በመከናወኑ ምክንያት በመጋዘን ውስጥ ዕቃዎች ተከማችተውና በርካታ ዕቃዎች ለረዥም ጊዜ ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- በበርካታ መ/ቤቶች መጋዘን ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ እቃዎች ከሚወገዱ እቃዎች ጋር ተቀላቅለው ተቀምጠው የሚገኙና የተለያዩ ኬሚካሎች፤ ጎማዎችና ሌሎች ዕቃዎች በወለል ላይ ለብልሽት በተጋለጠ ሁኔታ የተቀመጡ መሆኑ፣
- በአንዳንድ መ/ቤቶች ሠራተኞች መሥሪያ ቤቱን ሲለቁ የተረከቡትን የተለያዩ ቋሚ ዕቃዎች የማያስረክቡ መሆኑና የመንግሥትን ንብረት አጥፍተው በስራ ላይ በሚገኙ ሰራተኞች ላይም እርምጃ የማይወሰዱ መሆኑ፣
- በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ 173 ሰራተኞች ብር 1,594,818.71 የሚገመት ንብረት እና የገንዘብ ዕዳ እያለባቸው መ/ቤቱን የለቀቁ መሆኑ፣
- በግብርና ሚኒስቴር፤
  - ለረጅም ዓመታት ግምጃ ቤት ገቢ የተደረጉ፣ እና በተለይም በ1996 የተለያዩ መ/ቤቶች ሲዋሐዱ ተመላሽ የተደረጉ ንብረቶች በዓይነትና አገልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡት ሳይለዩ ለቁጥጥር በሚያስቸግር ሁኔታ ምንም ዓይነት ምዝገባ ሳይከናወን በተለያዩ 9 መጋዘኖች ለረጅም ጊዜ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣
  - በመሥሪያ ቤቱ ለረጅም ጊዜ የንብረት ማስወገድ ስራ ባለመስራቱ ምክንያት ብዛት ያለው ንብረት፤ የአገልግሎት ዘመን ያለፈባቸው ኬሚካሎች፣ የእንስሳት መድሃኒቶች እና ሰብሎች ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣
  - ቃሊቲ በሚገኘው የመሥሪያ ቤቱ መጋዘን በክልሎች ስም የመጡ የተለያዩ ብዛት ያላቸው የግብርና መሳሪያዎች፤ እንዲሁም በዕርዳታ የተገኙ ዘመናዊ ለግብርና ሥራ የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ ዕቃዎች ያለአገልግሎት ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ፣

➢ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ለተለያዩ ድርጅቶች በብድር የተሰጠ ብዛት 300 ኩንታል ሲሚንቶ፤ እንዲሁም ለጅማ ግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ በብድር የተሠጠ ቴራዞ የመሬት ምንጣፍ በቁጥር 1550 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤ በተጨማሪም በዩኒቨርሲቲው ለሚከናወኑ ጅምር ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚሆን ብዛት 64,400 ኩንታል ሲሚንቶ በተቋሙ ተገዝቶ ለስራ ተቋራጮች በዱቤ ሲከፋፈል እያንዳንዱ ሥራ ተቋራጭ የወሰደው ሲሚንቶ ብዛትና ዋጋ እንዲሁም ተቋራጩ ተመላሽ ያደረገው ወይም የከፈለው ገንዘብና የሲሚንቶው ብዛት መከታተያና መቆጣጠሪያ ስቶክ ካርድ/መዝገብ በማቋቋም ያልተመዘገበ መሆኑ፤ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

በመሆኑም የየመሥሪያ ቤቶቹ የንብረት አስተዳደር መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲመራ፤ በታዩት ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ፤ ተገቢ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በላክንላቸው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

ተሽከርካሪ

55. የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ ሁኔታ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል::

ሊብሬ ያልቀረበላቸው	በ15 መ/ቤቶች	221 ተሽከርካሪዎች
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	በ19 መ/ቤቶች	219 ተሽከርካሪዎች

መኖራቸው ታውቋል::

56. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ፣ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው፤ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ፣ በሊብሬው የተገለጸው ቁጥር በሞተር ላይ ካለው የተለያየ እና ሊብሬ ያልቀረበላቸው ደግሞ ጉዳዩ ተጣርቶ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡

መሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS)

ተከታታይ ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች

57. የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (PBS) ፕሮጀክት ተከታታይ (Continuous) ኦዲት በየሩብ ዓመቱ እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ሪፖርቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተልኮ ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ኦዲቱ የሚሸፍናቸው ሴክተሮች በወረዳና በክልል ደረጃ የሚገኙ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት፣ የውሃና የገጠር መንገድ ሴክተሮችን ነው፡፡

58. በዚህም መሠረት በ248 ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶችና የፕሮግራሙ ፈጻሚ የክልል ሴክተር ቢሮዎች ተከታታይ ኦዲት (Continuous Audit) እና አንድ ፕሮግራም አቀፍ የሆነ የማጠቃለያ (final audit) ኦዲት ለማካሄድ ታቅዶ በ262 ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶችና የፕሮግራሙ ፈጻሚ በሆኑ የሴክተር ቢሮዎች እንደዚሁም ፕሮግራም አቀፍ የሆነውን የማጠቃለያ (final audit) ኦዲት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ደረጃ በማካሄድ የPBS ኦዲቱን በታቀደው መሠረት ለመፈጸም ተችሏል፡፡

የክዋኔ ኦዲት ግኝቶች እና የማሻሻያ ሃሳቦች

59. የክዋኔ ኦዲት መሰረታዊ ተልዕኮ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች እና ድርጅቶች የተመደበላቸውን የሰው ሃይል፣ ገንዘብና ቁሳቁስ ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ በመጠቀም እንቅስቃሴአቸውን በብቃት በማከናወን የተሰጣቸውን ተልዕኮ ከግብ በማድረስ የሚጠበቀውን ውጤት ማስገኘታቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት አካሂዶ የታዩ ድክመቶች እንዲስተካከሉ ለስራ አመራሩ ተገቢውን የማሻሻያ ሃሳብ ማቅረብና ተፈጻሚነታቸውን በመከታተል ስኬታማ ውጤት እንዲገኝ መርዳት እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ነው፡፡

60. በዚሁ መሠረት ከጥር 2003 እስከ ታህሣሥ 2004 ድረስ ተጀምረው ወደ 2004/05 የኦዲት ዘመን የሚሻገሩ 5 ኦዲቶችን ጨምሮ 22 የክዋኔ ኦዲቶችን በማድረግ 17 ሪፖርት ለማውጣት ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት 17ቱም የክዋኔ ኦዲቶች ተጠናቅቀው ሪፖርቶቹ ወጪ ሆኗል፡፡ ሪፖርቶቹም በ17 ጥራዝ ተዘጋጅተው ለአፈ ጉባኤው ጽ/ቤት የተላኩ በመሆኑ የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎች የም/ቤት ቋሚ ኮሚቴ አባላት በሚገባ በመመርመር ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱ እያሳሰብን ዋና ዋና ግኝቶቹ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

__በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር በውጭ አገር ስለሚሠሩ ኢትዮጵያውያን የሥራ ሥምሪትና ደህንነት አጠባበቅ እና ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ተቀጥረው ስለሚሠሩ የውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ አሰጣጥ አስመልክቶ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት__

61. ለሥራ ወደ ውጭ አገር የሚሄድ ሠራተኛ የሥራ ውል በአሠሪው ተፈርሞ እና አሠሪው በሚገኝበት አገር የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት ቀርቦ ትክክለኛነቱ ሲረጋገጥ የሥራ ውሉ ለሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ቀርቦ መጽደቅ የሚኖርበት ቢሆንም በናሙና ከታዩት ወደ ኩዌት፣ ሳውዲ አረቢያ እና የተባበሩት አረብ ኢምሬት (ዱባይ) ለመሄድ የተዘጋጁ ሠራተኞች የሥራ ውል ውስጥ ወደ ሳውዲ አረቢያ የሚሄዱ ሠራተኞች የሥራ ውል በቀጣሪው ሳይፈረምና በኢትዮጵያ ኤምባሲ/ቆንስላ ሳይረጋገጥ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚጸድቅ መሆኑ፣

62. ለሥራ ሠራተኞችን ወደ ውጭ የሚልኩ በውጭ አገር ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች የላኩዋቸው ሠራተኞች የሥራ ፈቃድ ማግኘታቸውን በሄዱ በ15 ቀናት ውስጥ በአቅራቢያው ወደሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ/ቆንስላ አቅርበው ሊያስመዘግቡና ሠራተኞቹም የሥራ ፈቃድ ማግኘታቸውን እና በአቅራቢያው ባለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ቀርበው መመዝገባቸውን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት ማድረግ ሲጠበቅባቸው፣ የተወሰኑ የሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ሠራተኞቹን ወደላኩበት አገር ወደሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ/ቆንስላ ጽ/ቤት የላኳቸውን ሠራተኞ ዝርዝር ብቻ ሪፖርት እንደሚያቀርቡ ነገር ግን የሥራ ፈቃድ ማግኘታቸውን በአዋጁ በተጠቀሰው መሰረት በ15 ቀን ውስጥ እንደማያሳውቁ፣ ቀሪዎቹ የሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ደግሞ የላኳቸውን ሠራተኞች ዝርዝርም ሆነ የሥራ ፈቃድ ማግኘታቸውን በአቅራቢያው ላለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ሪፖርት የማያቀርቡ መሆኑ፣

63. ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ ሲጠየቅ ሥራው በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ሊሸፈን አለመቻሉ፣ በተጠየቀው መስክ ኢትዮጵያዊ ባለሙያ የሌለ ወይም እጥረት መኖሩ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት በቅድሚያ ፈቃድ የሚጠይቁት ድርጅቶች /አሠሪዎች እንዲያረጋግጡ ሳይደረግ ፈቃድ የሚሰጥ መሆኑ፡፡

በሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚ/ር የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ በሁሉም ዘርፍ ተካትቶ ተግባራዊ መደረጉን እና በሥርዓተ ጾታ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ በመፍጠር ውጤታማ ስለመሆኑን በተመለከተ የተካሄደ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

64. የስርዓተ ፆታ ጉዳይ በሁሉም ዘርፍ እንዲካተት በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ የስርዓተ ፆታ ማካተቻ መመሪያ (National Gender Mainstreaming Guide line) የተዘጋጀና በሰነዱ ላይ ከፌዴራል እና ከክልል ለተውጣጡ በሥርዓተ ፆታ ላይ ለሚሠሩ ሥልጠና የተሰጠ ቢሆንም ሰነዱ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ባዘጋጀው ሥልጠና ላይ የተሳተፉ ግለሰቦች ቢሰጥም፣ ለሴክተር መ/ቤቶች፣ ለክልሎች፣ ለዞኖችና ወረዳዎች ባለመላኩ በናሙና በተመለከትናቸው የፌዴራል፣ የክልል፣ የዞንና የወረዳ መ/ቤቶች የማይገኝ በመሆኑ የስርዓተ ፆታ ጉዳይ በሁሉም ዘርፍ በተቀናጀ መንገድ እንዳይካተት ማድረጉ፣

65. የስርዓተ ፆታ ጉዳይ በስትራቴጂዎች፣ በእቅዶች፣ በፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በመካተት ያስገኘው ውጤት የሚገመገምበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ሲሆን በናሙና ከተመረጡ የፌደራል መ/ቤቶች በግብርና ሚኒስቴር፣ በውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ በፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበር ኮንፌዴሬሽን የስርዓተ ፆታ ጉዳይ በስትራቴጂዎች፣ በእቅዶች፣ በፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች መካተቱና ተግባራዊነቱም ከዕቅድ እስከ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ የሚያከናውን ሲሆን የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፣ የፌደራል ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲና ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ የክትትልና የግምገማ ስርዓት የሌላቸው መሆኑ፣

66. ሴቶች ልማት ፈንድ አማካኝነት የገንዘብ ድጋፍ የተደረገላቸው የተለያዩ አካላት የልማት ፈንዱ ሥልጣንና ኃላፊነት ወደ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተላለፈ በኋላ ፈንዱን የወሰዱ የተለያዩ አካላት ያሉበትን የፋይናንስ ሁኔታ፣ ፈንዱን ለወሰዱበት ዓላማ ስለማዋላቸው ለማወቅ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግ ስለመሆኑ መረጃ ካለመቅረቡም በላይ ከሥርዓተ ጾታ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በተለያየ መልክ የሚገኙ ፈንዶች ምንጫቸውና ለምን ዓላማ እንደተገኙ የጊዜ ገደባቸውን ጨምሮ በሚገልጽ መንገድ ተለይተው ለመመዝገባቸውና ለመያዛቸው፣ ለታለመላቸው ዓላማና ተግባር መዋላቸው በክትትል የሚረጋገጥበት እና የሚገመገምበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ስለመደረጉም መረጃው ሊቀርብ አልቻለም፣

<u>በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን የዱር እንሰሳት ልማት፤ ጥበቃ እና አጠቃቀም በተመለከተ የተከናወነ የአካባቢ ኦዲት ሪፖርት</u>

67. በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ የዱር እንስሳት ብዛትና ስርጭትን ለማወቅ እንዲቻል አጠቃላይ ቆጠራ በመሬትና በአየር ለማድረግ የሚያስችል የበጀትና የማቴሪያል ድጋፍ የሚያስገኝ ሰነድ በ2000 በጀት ዓመት ለማዘጋጀትና ፈንድ ለማሰባበስብ በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም በዕቅዱ መሰረት ሰነዱ አለመዘጋጀቱና በአገሪቱ የሚገኙ የዱር እንስሳት አይነት፣ ብዛት እና ስርጭት ጥናቱም አለመከናወኑ፤

68. በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ሥር የሚተዳደሩ 11 ብሔራዊ ፓርኮች እና 2 የዱር እንስሳት መጠለያ ጣቢያዎች በድምሩ 13 የጥበቃ ቦታዎች ያሉ ቢሆንም ከእነዚህ ውስጥ ተከልለው ህጋዊ ሰውነት ያገኙት 3ቱ (የአዋሽ ብ/ፓርክ፤ የሰሜን ተራሮች ብ/ፓርክ እና የአላጥሽ ብ/ፓርክ) ብቻ መሆናቸውና ቀሪዎቹ 10 የጥበቃ ቦታዎች ህጋዊ ሰውነት የሌላቸው፤ ሕጋዊ ሰውነት ያገኘው የአዋሽ ብሔራዊ ፓርክም ይዞታው የአዋሽ ከተማ በፓርኩ ክልል ውስጥ እየተስፋፋና በሕገወጥ የቤት ግንባታና የመሬት ምሪት እየተካሄደበት ስለሆነ በዱር እንስሳቱና በመኖሪያ አካባቢያቸው ላይ ተጽዕኖ እየፈጠረ መሆኑ፤

69. ከዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ውጭ ያሉት የዱር እንስሳትና የመኖሪያ አካባቢያቸው የሚተዳደሩበት ደንብና መመሪያ መውጣት ሲገባው አለመውጣቱ፤

70. የባለስልጣኑ የዱር እንስሳት ውጤቶች እቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ከህገ ወጦች የተወረሱ ብዛታቸው በቁጥር 29,899 የሆነ የ320 የዱር እንስሳት ዓይነት ውጤቶች ተከማችተው የሚገኙ ሲሆን የዱር እንስሳት ውጤቶቹን በአግባቡ ለማስወገድ የሚያስችል አለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መመሪያ ባለሥልጣኑ ቢኖረውም፤ መመሪያውን መሰረት በማድረግ ውጤቶቹ እንዲወገዱ ባለመደረጉ እነኚህ የዱር እንስሳት ውጤቶች ለረጅም ጊዜ በመጋዘን ተከማችተው ለብልሽትና ለጉድለት በመጋለጥ ላይ መሆናቸው፤

<u>በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በአርብቶ አደር የዳልጋ ከብት ሀብት ልማት ላይ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት ሪፖርት</u>

71. በአርብቶ አደሩ አካባቢ የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋ ሊከሰት ከብቶችን ለመመገብና አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የመኖ ክምችትና መኖዎቹንም ለማከማቸት የሚያገለግሉ የመኖ ባንኮች በየወረዳው ሊቋቋሙ የሚገባ ቢሆንም የኦዲት ቡድኑ የመስክ ጉብኝት ባደረገባቸው በአፋር ክልል በገዋኔ፣ በአሳይታና በዱብቲ ወረዳዎች የመኖ ባንክ የተቋቋመ ሲሆን፣ በአፋምቦ ወረዳ አንድ የመኖ ባንክ የነበረ ቢሆንም አሁግ ግን አገልግሎት

መስጠት ማቆሙን፣ በኦሮሚያና በሱማሌ ክልል አርብቶ አደር ወረዳዎች የመኖ ባንኮች የሌሉ መሆኑንና በዕቅድ ደረጃ እንኳን ለማቋቋም የታሰበአለመሆኑን፤

72. የግጦሽ መሬቶች ላየ አላስፈላጊ አረሞች በስፋት ማታየታቸውና ችግሩንም ለማስወገድ የሚያስችሉ የመፍትሄ ሃሣቦች በመዘግየታቸው በአርብቶ አደሩ አካባቢ ላሉ የዳልጋ ከብቶች የሚሆነውን የግጦሽ መሬት እንዲያንስና የመኖ እጥረት እንዲከሰት ማድረጉ፤

<u>በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የመንገድ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት ሪፖርት</u>

73. የመንገዶች ግንባታ፣ ማጠናከሪያ እና ማሻሻያ ፕሮጀክቶች የመምረጫ መስፈርት በዋነኛነት ለእድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱትን የኢኮኖሚ ዘርፎች (ግብርና፣ ማእድን፣ ቱሪዝም፣ ኢንዱስትሪ ....) በመለየት ቅድሚያ ሊሰጥ የሚገባ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከተመረጡት ፕሮጀክቶች ውስጥ፤ ለኮምቦልቻ - ወልዲያ፣ ዛሪማ - ማይጸምሪ፣ መካነ ሰላም - ግንደወይን፣ ዱር ቤቴ - ሻሁራ፣ ጎንደር - ደባርቅ፣ ሐረር - ጂጂጋ፣ ዛሪማ - ማይጸምሪ፣ ማይጸምሪ - ሺሬ፣ ማይጸምሪ - ዲማ፣ ሞጆ- አረርቲ፣ ቡታጂራ- ጉብሬ፣ ሁምቦ አርባ - ምንጭ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክቶች በመንገድ ሴክተር ዴቨሎፐመንት ፕሮግራም በተቀመጡ መስፈርቶች መሠረት ተመልምለው የተመረጡ ስለመሆኑ ማስረጃ ሊቀረብ አልቻለም፡፡

74. ለማንኛውም የመንገድ ግንባታ፣ ማሻሻያ እና ማጠናከሪያ ፕሮጀክት የተሟላ ዝርዝር የኢንጂንሪንግ ዲዛይን ጥናት በቅድሚያ በማከናወን የመንገድ ሥራውን መጠን፣ መንገዱ የሚያልፍበት አቅጣጫና ወሰን፣ በአካባቢው የሚገኙ የግንባታ ቁሳቁስና አይነት በመለየት፣ የአካባቢውን የአየር ሁኔታ፣ ሀይድሮሎጂ እና ጂኦሎጂ በማወቅ፣ በአጠቃላይ የፕሮጀክቱ ዋጋ እና ግንባታው የሚፈጀውን ጊዜ ከወዲሁ ማወቅ የሚቻል ቢሆንም፤ በናሙና ተመርጠው በታዩት የሐረር - ጂጂጋ፤ ሁምቦ-አርባ ምንጭ፤ ኮምቦልቻ - ወልዲያ፤ ጎንደር - ደባርቅ፤ ማይጸምሪ - ዲማ፤ ጎሬ-ጋምቤላ መንገዶች ከዲዛይን ክለሳ ጋር በተያዘና በተቀመጠው መርሀ-ግብር ባለመጠናቀቃቸው ከ880 ሚሊዮን ብር በላይ ተጨማሪ ወጪ ማስከተላቸውና አሁንም አብዛኛዎቹ መንገዶች አለመጠናቀቃቸው፤

<u>በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የህንፃና የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ደረጃና ቁጥጥርን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት</u>

75. በሚኒስቴር መ/ቤቱ በግንቦት ወር 2003 ዓ.ም ተዘጋጅቶ የፀደቀው የህንፃ መመሪያ ቢኖርም በናሙና በታዩት በአዳማ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤትና በይርጋለም ከተማ

ማዘጋጃ ቤት የህንፃ መመሪያው ያልደረሰ መሆኑ፣ ነገር ግን ሰነዱ የደረሳቸው የአዳማ፣ ሻሸመኔ፣ ባህር ዳርና ሀዋሳ ከተማ ማዘጋጃ ቤቶች ኃላፊዎች በሠነዶቹ ላይ የወሰዱትን የግንዛቤ ማስጨበጫ በሥራቸው ላሉ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ያላስተላለፉና ወደ ትግበራ ያልገቡ መሆናቸው፤

76. በሚኒስቴር መ/ቤቱ በግንቦት 2003 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ የጸደቀው የህንጻ መመሪያ የፊት መስታወት ዓይነት (mirror glass) ወይንም ተመሳሳይ ውጤት እንዲኖረው የተደረገ መስታወት ለግንባታ የውጭ አካል አገልግሎት መጠቀም እንደማይቻልና በህንፃ የውጭ መስኮቶች አንፀባራቂነት የነዋሪውን ደህንነትና የትራፊክ እንቅስቃሴ ማወክ እንደሌለበት ቢገለጽም፤ በናሙና በታዩት የአዳማ፣ የሻሸመኔና የባህር ዳር ማዘጋጃ ቤት እንዲሁም በባህር ዳር ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት በህንፃዎች ላይ የሚገጠሙ መስታወቶች ከውበት አንፃር እንጂ የአካባቢ ብክለት የማያስከትሉ፣ ሙቀት የማይፈጥሩና አንፀባራቂ አለመሆናቸው የማይረጋገጥ መሆኑ፤

77. ማንኛውም የሕንፃ ግንባታ ሥራ በሚከናወንበት ወቅት በግንባታ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሠራተኞች የደህንነት መጠበቂያዎችን ማሟላት የሚገባቸው ቢሆንም በኦዲቱ በናሙና በታዩት የአዲስ አበባ፣ ይርጋለም፣ ሀዋሳ፣ ሻሸመኔ፣ አዳማና ባህር ዳር ሁሉም የግንባታ ሳይቶች የግንባታ ሰራተኞች ለሥራ ሲሰማሩ የደህንነት መጠበቂያዎችን እንደማይጠቀሙ መረጋገጡ፤

በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት የመንገድ ፈንድ አስተዳደርን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

78. ክብደት ላይ የተመሠረተ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ ገቢ ለመሰብሰብ የሚያስችል ደንብና መመሪያ ተዘጋጅቶ ባለመጽደቁ ጽ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 66/89 መሰረት ከዚህ ምንጭ ገቢ መሰብሰብ የሚኖርበት ቢሆንም ከተመሰረተ ጊዜ ጀምሮ ገቢውን አለመሰብሰቡና የተባለው ደንብና መመሪያም እስከ አሁን አለመውጣት ተገቢ አለመሆኑ፤

79. ጽ/ቤቱ ለመንገድ ጥገና እና ደህንነት ፈንድ ሲሰጥ ገንዘቡ ለታቀደለት ፕሮጀክት በትክክል ስራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ከ2001 እስከ 2003 በጀት ዓመት ለአማካሪ ድርጅቶች የብር 39.97 ሚሊዮን ክፍያ የፈጸመ ቢሆንም፤ አማካሪ ድርጅቶቹ በበኩላቸው ኃላፊናታቸውን እየተወጡ ስለመሆኑ በናሙና ሲጣራ፣ በወሊሶ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ይህንኑ ለመከታተል የተቀጠሩ አማካሪ ድርጅቶች የክትትልና የቁጥጥር ሥራውን በአግባቡ እየሠሩ አለመሆኑን፣ በኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን አማካሪ ድርጅቶቹ በተባሉበት ቦታ የማይገኙ እና

ክትትልም የማያደርጉ መሆኑንና በአማራ ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን አማካሪ ድርጅቶቹ ያላቸው የሰው ኃይል ከሚሠራው ሥራ ጋር ተመጣጣኝ ስላልሆነ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ የሚፈለገውን ያህል እንዳልሆነ መገለጹ፤

80. በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የተዘጋጀ የመንገድ ጥገና ደረጃ ቢኖርም፣ መሠረታዊ የመንገድ ጥገና ደረጃን ተከትለው የመንገድ ጥገና ሥራዎች ወጥ (standardize) በሆነ መንገድ እንደማይከናወን በናሙና ከተመረጡት የኦሮሚያ፣ የአዲስ አበባ፣ የደቡብ መንገዶች ባለሥልጣን፣ እና የአማራ ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን እንዲሁም ከባህርዳር፣ ከጐንደር፣ ከሀዋሣ፣ ከጅማ፣ ከወሊሶ እና ከወልቂጤ ከተማ ማዘጋጃ ቤት መረዳት ከመቻሉም በላይ በመንገድ ጥገና ደረጃ መሠረት ለጥገና የሚጠቀሙበት ግብዓት እና ፕሮጀክቱ የሚወስደው ጊዜ ተወስኖ ተግባራዊ ባለመደረጉ እንዲሁም አማካሪ ድርጅቶችም ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል ሳያደርጉ ተሰራ ተብሎ የቀረበውን የክፍያ ሰርተፊኬት ያለገደብ የሚያረጋግጡ በመሆኑ በርካታ ፕሮጀክቶች በጊዜ እና በዋጋ ከዕቅድ በላይ መሆናቸው፤

<u>በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር በውጭ ድጋፍ/እርዳታ እና በፌዴራል ደረጃ የሚስተባበሩ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች አፈፃፀም በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት</u>

81. የውሃ ልማት ፈንድ ፅ/ቤት በአጠቃላይ ከሚያገኘው ፈንድ ውስጥ እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ ከ30% በላይ ተጠቅሞ የማውያቅ ሲሆን በ2003 በጀት ዓመት የተጠቀመው 51% ብቻ መሆኑ፡

82. በጽ/ቤቱ ከሚስተባበሩ የከተማ የመጠጥ ፕሮጀክቶች ውስጥ የተጠናቀቁት የሚዛን ተፈሪ፣ የወልቂጤ፣ የሃዋሳ እና አክሱም ከተማ ፕሮጀክቶች ሲሆኑ እነዚህም ፕሮጀክቶች ቢሆን የተጠናቀቁት እያንዳንዳቸው ከአንድ ዓመት በላይ ዘግይተው ሲሆን የሐረር እና የክብረመንግስት ከተሞች ስራቸው እስከ መስከረም 2004 ዓ.ም ሙሉ በሙሉ ያልተጠናቀቀ ሲሆን መጠናቀቅ ከነበረባቸው ጊዜ በላይ 6 እና 4 ዓመት እንደየቅደመ ተከተላቸው መዘግየታቸው ታውቋል፡፡

83. የምንዛሪ ጭማሪን አካቶ በጠቅላላው IDA/DFID ከተያዘው ብር 3.4 ቢሊዮን ውስጥ ፕሮግራሙ ከተጀመረ ከ6 አመት ተኩል በኃላ እና ለመጠናቀቅ አንድ አመት ተኩል /19%/ ሲቀረው ስራ ላይ የዋለው ብር 1.17 ቢሊዮን (34.6%) ብቻ መሆኑ፤

84. በADB የሚደገፈው የንፁህ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት መጀመሪያ እንዲጠናቀቅ ታሰቦ የነበረው በ4 ዓመት ውስጥ ሲሆን በዋጋ ንረት እና በተለየዩ ምክንያቶች ወደ 6 ዓመት ተራዝሟል፡፡

ይሁንና ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ከ4 ዓመት ተኩል በኋላ ለፕሮጀክቱ ከተያዘው ጊዜ ውስጥ 25% እየቀረው ጥቅም ላይ የዋለው ገንዘብ ለፕሮጀክቱ በምንዛሬ ጭማሪ የተገኘውን አካቶ ካለው አጠቃላይ ብር 1.01 ቢሊዮን በጀት ውስጥ ብር 213.41 ሚሊዮን (21%) ብቻ መሆኑ፤

<u>ለህብረት ሥራ ማህበራት ድጋፍ ለመስጠት የተዘረጋውን የአሰራር ስርዓት አፈፃፀምን ውጤታማነት በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት</u>

85. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ አገር አቀፍ የህብረት ስራ ፖሊሲ በማዘጋጀት እስከ 2003 ዓ.ም ድረስ ለማስፀደቅ ዕቅድ የያዘ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ የህብረት ስራ ፖሊሲውን አለመቅረጹ፤

86. ኤጀንሲው በመላ አገሪቱ ለሚገኙ ኅብረት ሥራ ማህበራት አንድ ወጥ የሆነ የሂሣብ ምርመራ /ኦዲት/ ማድረጊያ ጊዜ ባለመዘርጋቱና ተግባራዊ ባለማድረጉ በአማራ፣ በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያ እና በደቡብ ከተደራጁ የህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ በ2001 25,155 (80.8%)፣ በ2002 26,837 (77.7%)፣ በ2003 31,267 (84.2%) የሚሆኑት የኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት ያለመደረጋቸው፣ ነገር ግን ኤጀንሲው በራሱ ባለሙያዎች ኦዲት ያደረገውን የኦዲት ሪፖርት ለሕብረት ስራ ማህበራት ጠቅላላ ጉባኤ አስቀርቦ የማያጸድቅ፣ በኦዲት ሪፖርት የተሰጡ አስተያየቶችን ተግባራዊነትም መርሀ ግብር ነድፎ የማይከታተል መሆኑ፤

<u>መንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድን በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት</u>

87. ወደ ባለአደራ ቦርዱ ከተላለፉና በናሙና ከታዩት 13 የተለያዩ መጋዘኖች፣ ሱቆችና ቢሮዎች ውስጥ 12ቱ (92%) ዋጋቸው በወቅቱ የገበያ ዋጋ መሰረት ሳይከለስና የሥራ አመራር ቦርዱ ሳይፈቅድ ከ1997 እስከ 2004 እየተከራዩ መገኘታቸው፤

88. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ባለአደራ ቦርዱ ከተረከባቸው የተለያዩ ንብረቶች ውስጥ የአዲስ መለዋወጫ ዕቃዎች አስመጪና አከፋፋይ አክሲዮን ማህበር እና የቀድሞው የኢትዮጵያ ችርቻሮ ንግድ ኮርፖሬሽን ንብረቶች በአንድ መጋዘን ውስጥ ንብረቶቹን በከፊል በቦታ በመለየት ጥበቃው በሌላ አካል ስር ሆኖ ከላይ ክፍት በሆነ ቦታ መቀመጣቸውን፤ እንዲሁም ባለአደራ ቦርዱ ንብረቶቹን ከተረከበ ጊዜ ጀምሮ ለመኖራቸው (Existance) የማረጋገጥ ስራ ተሰርቶ የማያውቅ መሆኑ፤

89. በሽያጭ ይዞታቸው ከተላለፉና በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ድርጅቶች ውስጥ አቃቂ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ብር 35.14 ሚሊዮን የመነሻ ዋጋ ሲሰላ ባለው እዳ እና

ወደፊት ስራዎችን ለማከናወን ሊወጡ የሚችሉ ወጪዎችን ታሳቢ በማድረግ የተሰጠ እንጂ የድርጅቱ ንብረት በባለሙያ ተጠንቶ የጨረታ መነሻ ዋጋ ያልተሰጠ መሆኑ እና ጨረታ ሲወጣ የጨረታ ሰነድ ዝርዝር ላይ የነዳጅ ማደያና ዲፖ ዝርዝር ውስጥ ያልተካተተ እና ዋጋ ያልተሰጠበት መሆኑ፤

90. እንደዚሁም የቡና ግዥና ሽያጭ ድርጅት ለጨረታ የቀረቡ 13 የቡና ማበጠሪያዎች፣ ጽ/ቤቶች እና መጋዘን የዋጋ ግምት በባለሙያ አለመታየቱና የጽ/ቤቶች የቡና ማበጠሪያዎች በውስጣቸው የያዙት የማበጠሪያ ማሽን፣ የቋሚ ንብረት ብዛት እና አይነት ሳይገለፅ የመነሻ ዋጋ የተሰጣቸው መሆኑ፣ የዲላ ጽ/ቤት ኤ(A) ሽያጭ ተፈፅሞ ለገዥው ርክክብ ሲደረግ ወደገዥው መተላለፍ ከነበረበት ንብረት ውስጥ 52 አይነት ቋሚ ንብረት ያልተላለፈ መሆኑ እንዲሁም የቡና ግዥና ሽያጭ ድርጅት የጌምቤ ጽ/ቤትና መጋዘን በብር 555,000 ጨረታውን ካሸነፉ በኋላ ዋጋ የተሰጠው በስህተት ነው በማለት አሸናፊው ለዋስትና ባስያዘው ብር 55,000 ከጨረታ መነሻ ዋጋ በ45% አንሶ የተሸጠ መሆኑ፤

<u>በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ምግብና ምግብ ነክ</u>

<u>ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶች አጠባበቅን በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት</u>

91. በአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር በሚገኙ መጋዘኖች እህል ገቢና ወጪ ሲደረግ መመዘን ሲኖርበት በናሙና በታዩት በወላይታ ሶዶ፣ በሽነሌና በወረታ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች እህል ወደ መጋዘን ገቢና ወጪ ሲደረግ በምድር ሚዛን የማይመዘን መሆኑ፤

92. አስተዳደሩ ለስራው አስፈላጊ በመሆናቸው በግዥና በእርዳታ ያገኛቸውን የእህል ሚዛኖች በአግባቡ ስራ ላይ ሊያውል፣ ሲበላሹም በወቅቱ ሊያስጠግን እና መጠገን ካልቻሉም የሚወገዱበትን መንገድ ማመቻቸት ሲኖርበት፤ በእርዳታ ያገኛቸው አገልግሎት የማይሰጡ ተንቀሳቃሽ የእህል ሚዛኖች በወቅቱ እንዲጠገኑ ወይም መወገድ የሚገባቸውን እንዲወገዱ አለማድረጉ፤

93. አስተዳደሩ ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሰቁሶች ለሚፈለጉበት ተግባር በብድርና በትውስት ለመስጠት የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት ክምችቱን በአግባቡ እንዲጠበቅና ለጉዳት እንዳይጋለጥ መጠበቅ ሲኖርበት በአስተዳደሩ የአዳማ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች መጋዘን ውስጥ ለረዥም ጊዜ ያለአገልግሎት መከማቸታቸው እና በክምችቱም ውስጥ ለጉዳት የተጋለጡ ቁሰቁሶች መኖራቸው፤

<u>በትምህርት ሚኒስቴር በቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የውጤት ተኮር ስልጠና እና የቴክኖሎጂ ሽግግርና ክምችት ስርአት ውጤታማነት በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት</u>

94. በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ፣ የክልል ቢሮዎች እንዲሁም የማሰልጠኛ ተቋማትና ኮሌጆች የሥራ ገበያ ፍላጐት ጥናት በማጥናት ስልጠናውን ማካሄድ ሲገባ፤ በናሙና የታዩት በአማራ እና ኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሥራ ገበያ ፍላጎት ጥናት ቢያካሄዱም በጥናቱ መሠረት ሥልጠና የማይሰጡ መሆኑ እና በአዲስ አበባ መስተደደር ሥር የሚገኙ የቴክኒክ ሙያ ተቋማት ደግሞ የሥራ ገበያ ፍላጎት ጥናት የማያካሄዱ መሆኑ፤

95. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ሰልጣኞች የስልጠና ጊዜያቸውን 70%ቱን በኢንደስትሪ ውስጥ በተግባር ልምምድ 30%ቱን ደግሞ በንድፈ ሃሣብ ስልጠና እንዲያሳልፉ ክትትል ማድረግ ሲጠበቅቸው በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በአማራ፣ በኦሮሚያና የአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ አብዛኛዎቹ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት በኢንደስትሪና የግንዛቤ እጥረት ምክንያት 70%ቱን በኢንደስትሪ ውስጥ የትብብር የተግባር ስልጠና በተሟላ መልኩ አለመተግበሩ፤

<u>በምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን የመድኃኒት ጥራት፣ ደህንነት፣ አጠቃቀም እና አወጋገድ በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት</u>

96. ባለስልጣን መ/ቤቱ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስፈላጊውን የጥራት መመርመሪያ መሣሪያዎችን እንዲሁም በመግቢያና መውጫ ኬላዎች ላይ የሚኒ እና የተንቀሳቃሽ (mobile) ላብራቶሪዎችን በማደራጀት ስራ ላይ ማዋል ሲኖርበት በኬላዎችና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የጥራት መመርመሪያ የሚኒና ተንቀሳቃሽ ላብራቶሪዎች አለመሟላታቸው፤

97. በኢንስፔክሽን ውጤት መሰረት ባለስልጣን መ/ቤቱ ደንብን በተላለፉ ድርጅቶችና ግለሰቦች ላይ ተመጣጣኝ እና ወጥነት ያለው እርምጃ መውሰድ የሚያስችል ደንብ በማውጣት ሥራ ላይ ሊያውል ሲገባ፤ ደንቡን አለማውጣቱ፤

98. ባለስልጣን መ/ቤቱ የመድኃኒት አጠቃቀም ቁጥጥር መመሪያ በማዘጋጀት ስራ ላይ ማዋል ሲኖርበት፣ መመሪያውን አለማዘጋጀቱና ሥራ ላይ አለማዋሉ፤

99. የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን የሚያስመጡና የሚያከፋፍሉ ድርጅቶች መድሐኒቶቹን ለመጠበቅ የሚያስችል ባለቁልፍ የብረት ካቢኔት ያላቸው መሆኑን

ባለስልጣኑ ማረጋገጥ ሲጠበቅበት የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድሐኒቶች ከብረት ካቤኔት ውጭ እንደማንኛውም መድሐኒት በመደርደሪያ ላይ መቀመጣቸው፤

100.ባለስልጣን መ/ቤቱ የባህል መድኃኒቶችን ደህንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት ለማረጋገጥ የሚያስችል የመቆጣጠሪያ ስርዓት ሊዘረጋ፣ ምዝገባ በማካሄድ የምስክር ወረቀት ሊሰጥና ባህላዊ ሕክምና አገልግሎት ከዘመናዊው ህክምና ጋር ተቀናጅቶ ሊሠራ የሚችልበትን ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ የሚጠበቅበት ቢሆንም እስከአሁን ሥርዓቱን አለመዘርጋቱ፤

<u>የብዝሀ ሕይወት ሀብት አጠባበቅ እና አጠቃቀምን በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት</u>

101.ሀገር በቀል የሆኑ በተለይም ዝርያቸው በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ የብዝሀ ህይወት ሀብቶች ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊጠበቁ እና ሊስፋፉ የሚችሉበት ሁኔታ ሊመቻች የሚገባ ቢሆንም የነዚህ የነባር ዝርያዎች ልዩ ጠቀሜታን በተመለከተ በኅብረተሰቡ ዘንድ ያለው ግንዛቤ እንዲዳብር ባለመደረጉ ዝርያዎቹ በከፍተኛ ሁኔታ እየተመናመኑ እና እየቀነሱ እንዲሁም የአካባቢው ባልሆኑ ሌሎች ዝርያዎች እየተተኩ መሆኑን፤

102.በኢዘቦታ (exsitue) ወይም ከተፈጥሮ የአኗኗር ሁኔታ ውጪ በናሙና ተይዘው በማቀዝቀዣ ክፍል ውስጥ በመጠበቅ ላይ የሚገኙ ዕጽዋቶች ከአቅም በላይ በሆኑ ድንገተኛ አደጋዎች (እሳት አደጋ፣ ጎርፍ፣ ወዘተ) እንዳይጎዱና እንዳይጠፉ ለመጠበቅ እንዲቻል ተመሳሳይ ናሙናዎች በሌላ ቦታ (duplicate gene bank) ሊጠበቁ የሚገባ ቢሆንም በኢንስቲትዩቱ ሥር በኢዘቦታ (ጅን ባንክ) የብዝሀ ህይወትን መጠበቂያ ስፍራ አንድ ብቻ ስለሆነ ባልተጠበቀ ሁኔታ አደጋ ቢደርስ ኪሳራው ሊካካስ የማይችል እና ከፍተኛ ጥፋት ሊደርስ የሚችል መሆኑ፤

103.የውጭ ሀገር ተመራማሪዎች ወይም ተቋማት የዘረመል ሀብት አርከቦት ጥያቄ አቅርበው ሲፈቀድላቸው ወደ ሥራ በሚገቡበት ወቅት ህጋዊነትን ያልተከተለ ተግባር እንዳይፈጽሙ ለመከላከል የሚያግዝ የአሠራር ሥርዓት ሊኖር እና ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ቢሆንም የውጭ ተመራማሪዎች ፈቃድ አግኝተው በብዝሀ ሕይወት ሀብት ዙሪያ ጥናት በሚያደርጉበት እና መረጃ በሚሰበሰቡበት ወቅት ከማስተባበር ውጪ ኢትዮጵያዊያን ባለሞያዎችን አብሮ በመሳተፍ የቅርብ ክትትል የማድረግ ተግባር ተገቢው ትኩረት ያልተሰጠው በመሆኑ የጄኔቲክ ሀብት ስርቆት ሊደርስ የሚችልበት ዕድል ሰፊ መሆኑ፤

104.ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በተለያየ መንገድ ወደ ውጪ የተወሰዱ የብዝሀ ህይወት ሀብቶች ጥቅምን የመጋራት ወይም የማስመለስ ተግባራትን የሚመለከቱ የሕግ ጉዳዮችን በመከታተል ሀገሪቱ ከብዝሀ ሕይወት ሀብቷ የተሻለ ተጠቃሚ እንድትሆን ጥረት ሊደረግ የሚገባ ቢሆንም በኢንስቲትዩቱ ብዝሀ ሕይወትን የሚመለከቱ የሕግ ጉዳዮችን የሚከታተል አካል አለመኖሩ፤

<u>ኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የመንገዶች አጠባበቅ እና ጥገናን በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት</u>

105.በባለስልጣኑ ሥር የሚተዳደሩ መንገዶች ከመጀመሪያ ግንባታቸው ጀምሮ በየጊዜው የተደረገላቸውን የጥገና ሂደት ታሪክ (Road History) ለአጠቃቀም በሚያመች እና ግልጽ በሆነ ሁኔታ በመረጃ ቋት ሊያዝ የሚገባ ቢሆንም በናሙና በተመረጡ ዲስትሪክቶች በተደረገ የመስክ ጉብኝት ከተሰበሰቡ መረጃዎቸ ባለሥልጣኑ ለሚያስተዳድራቸው መንገዶች ከመጀመሪያ ግንባታቸው ጀምሮ አጠቃላይ ታሪካቸውን የሚያሳይ የመረጃ ቋት (Road History) የማይያዝላቸው መሆኑን፤

106.የመንገድ ጥገና ከመከናወኑ አስቀድሞ የጥገና ዕቅድ ሊዘጋጅ፤ የመንገድ ጥገና እቅድ በሚዘጋጅበት ወቅትም የመንገዱን የመጀመሪያ ፕላን፣ ከዚህ ቀደም በመንገዱ ላይ የተካሄዱ የጥገና ሥራዎች እና በእነዚህ ጥገናዎች ወቅት የተገኙ ግኝቶች ወዘተ… ታሳቢ ማድረግ ያለበት ቢሆንም ለጥገና ከሚመደበው በጀት ዝቅተኛነት የተነሳ የሚከናወነው የጥገና ሥራ በዕቅዱ መሠረት እንዳልሆነ በሚመደበው በጀት መጠን ቅድሚያ ሊሰጣቸው ለሚገቡ መንገዶች ብቻ ጥገና የሚደረግ መሆኑ፤

107.የመንገዶች ግንባታ እንደተጠናቀቀ ለመንገዶቹ አስፈላጊው ወጥነት እና ተከታታይነት ያለው ጥበቃ እና ጥገና ሊደረግላቸው የሚቻልበት ሁኔታ ሊመቻች የሚገባ ቢሆንም የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ የሆኑት ዲስትሪክቶች የሚያስተዳሩት የመንገድ አውታር ሽፋን ካላቸው የሠራተኛ ብዛት እና ከሚመደበው በጀት ጋር የማይጣጣም መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከአካባቢው መስተዳደር ጋር ተቀናጅቶ የሚሠራበት ሁኔታ አጥጋቢ አለመሆኑን እና በተለይም ለመንገድ ጥገና የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ከአካባቢው ለማግኘት እንዲሁም ዋና መንገዶችን እና የመንገድ ዳር ይዞታዎችን ለማስጠበቅ በሚደረጉ ሂደቶች ላይ የጎላ ችግር መታየቱ እንዲሁም በመንገድ ዳር ሀብቶች (ምልክቶች) ላይ ስርቆት እየተፈጸመ መሆኑን፤ ለመንገድ ዳር ቦዮች እና ፍሳሽ ማስተላለፊያዎች ወቅታዊ እንክብካቤ አለመደረጉ፤

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

108.በአጠቃላይ እያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊ በክዋኔ ኦዲት ግኝቶች ላይ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ድክመት የታየባቸውን አሠራሮችና አፈጻጸሞች እንዲያሻሽል ተገቢው ምክርና የማሻሻያ አስተያየት የተሰጠቸው ሲሆን ም/ቤቱም የተጠናከረ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የመንግሥት መ/ቤቶች ተልዕኮአቸውን በተሻለ ሁኔታ እንዲወጡ ሊያግዝ ይገባል፡፡

የፌዴራል የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ

ሂሣብ ኦዲት በተመለከተ

109.በገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ የሚቀርብ የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ የ2003 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት የተከናወነ በመሆኑ፣ ውዝፍ የኦዲት ሥራ የሌለ ሲሆን የ2003 በጀት ዓመት የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

110.በ2003 በጀት ዓመት ከብድር ፋይናንስ የተገኘ ገንዘብ በዓመታዊ ገቢና ወጪ የሂሳብ መግለጫ ላይ መካተቱንና በበቂ መረጃ መደገፉን ለማረጋገጥ ኦዲት በሚደረግበት ወቅት ከተጠቃሚ መስሪያ ቤቶቹ ገንዘቡ ለመድረሱ መረጃ ሳይኖር ከብድር አስተዳደር በተገኘ መረጃ ብቻ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል እና አዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ስም ብር 764,527,143.27 ተመዝግቦ መገኘቱ፣

111.በተለያዩ ምክንያቶች በስህተት የተሰበሰበ ቀረጥና ግብር በስህተት መሰብሰቡ በኮሚቴ ሲረጋገጥ በበጀት ተይዞ ለግብር ከፋዩ ተመላሽ የሚደረግ ሲሆን ተመላሽ የተደረገው የቀረጥ መጠን ግን በገቢ ሪፖርት ተመዝግቦ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እየቀረበ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ይህንኑ ሂሳብ እያጠቃለለ ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል በስህተት ለተሰበሰበ ቀረጥ ተመለሽ የሚሆን በጀት እየተያዘና ክፍያም እየተፈጸመ ያለው በሂሳብ መደብ 6412 ለተቋሞች እና ድርጅቶች የሚደረግ ድጋፍና ድጎማ በሚመዘገብበት የሂሳብ መደብ ሲሆን በ2003 በጀት ዓመት በዚህ መልክ ብር 109.62 ሚሊዮን በበጀት ተይዞ ክፍያ ተፈጽሟል፡፡ አሠራሩ የገቢ ሪፖርት ከፍ እንዲል (overstated)፣ ያልተሰጠ ድጋፍና ድጎማ እንደተሰጠ በማመልከት ሪፖርቱን የሚያዛባ በመሆኑ ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ አሳሰበናል፡፡

112.በተጠቃለለው የ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ በሂሳብ መደብ 4210 ብር 47.43 ሚሊዮን የሚታይና ጉዳዩ ሲጣራ በ L/C ባንክ ሂሳብ ቁጥር 01601/012850/00 ከ1995 ጀምሮ በሂሣብ መደብ 4418 አላቂ ዕቃ በሚመዘገብበት አርዕስት የሚታይ ሲሆን በዚህ ገንዘብ

ከውጭ የሚገዛ ዕቃ ለመኖሩ ማስረጃ እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ ባለመቻሉ ክትትል ተደርጎ ገንዘቡ በአስቸኳይ ወደ መንግሥት ካዝና ተመላሽ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

የኦዲት ማሻሻያ ሃሣቦች ላይ የማስተካከያ እርምጃ

ስለመወሰዱ የሚደረግ ክትትልን በተመለከተ

113.የ2002 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ላይ የተሰጡ የማሻሻያ አስተያቶች በተመለከተ ኦዲት ተደራጊዎች ባለፈው ዓመት ባዘጋጁት መርሃ ግብር መሰረት እርምጃ ስለመውሰዳቸው በ2003 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅት በተደረገ ክትትል መሻሻል የታየ ቢሆንም፤ ኦዲት ተደራጊዎች አሁንም የተጠናከረ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ የ2003 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት እንደተጠናቀቀ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች ለተገኙባቸው 67 የፋይናንስና ህጋዊነት እና 17 የክዋኔ ኦዲት የተካሄደባቸው መ/ቤቶች የማስተካከያ መርሃ-ግብር ነድፈው እንዲያሳውቁን ጥያቄ የቀረበ ቢሆንም፤ ይህ ሪፖርት እስከሚጠናቀር ድረስ መርሀ-ግብሩን የላኩት 29 መ/ቤቶች ብቻ ናቸው፡፡ ያለበቂ ምክንያት በፌዴራል ዋና ኦዲተሩ በቀረቡ የኦዲት ሪፖርቶች በተሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶችና ሃሣቦች ላይ በወቅቱ እርምጃ ያለመውሰድ የሕግ ተጠያቂነትን የሚያስከትል መሆኑ ታውቆ የእያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ ም/ቤቱም በዚህ ረገድ የሚያደርገውን ክትትልና ቁጥጥር ማጠናከር ይኖርበታል፡፡

የሪፎርም ሥራን በተመለከተ

114.በመ/ቤታችን የውጤት ተኮር የምዘና ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ ጥናቱ የተጀመረ ሲሆን በቅርቡ እንደሚጠናቀቅና ከ2005 በጀት ዓመት መጀመሪያ አንስቶ ተግባራዊ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡

115.ከሪፎርሙ ተከትሎ የተተገበሩ አዳዲስ አሰራሮችን በመረጃ ቴክኖሎጂ ለማስደገፍ የተጀመረው ጥረት የመረጃ ቴክኖሎጂ ዕቃዎች ግዥ ከመጠን በላይ በመዘግየቱ በዕቅዱ መሰረት በፍጥነት ሊተገበር አልቻለም፡፡ ሆኖም በአሁኑ ወቅት ሂደቱን ለማፋጠን ጥረት በመደረግ ላይ ነው፡፡

116.የሰው ሀብት ልማት ሥራውም የሰው ሀብት ልማት ስትራቴጂውን ተከትሎ በመከናወን ላይ ሲሆን ትልቁ ፈተና ግን የሰው ሀብት ልማትና መደበኛ ሥራን ማጣጣምና አቅሙ የተገነባውን ሠራተኛ ማቆየት የመቻሉ ጉዳይ በመሆኑ ም/ቤቱ ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ሴክተር ዘለል የሆኑ ሥራዎች በተመለከተ

117.በሥርዓተ ጾታ፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እና የአከባቢ ጥበቃ ዙሪያ ከተከናወኑት ተግባራት፣

- በስርዓተ ጾታ ተወካይና በመ/ቤቱ የሴቶች ጉዳይ ኮሚቴ አስተባባርነት በተደረገ እንቅስቃሴ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ለሶስተኛ ጊዜ በመ/ቤታችን የማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን እንዲከበርና በተጋባዥ የሴቶች ጉዳይ ባለሙያ በቀረበ የሥርዓተ ፆታ ትምህርት ሠራተኛው ግንዛቤ እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡
- ለ34 የመ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የ Gender Mainstreaming በሥርዓተ-ጾታና ልማት፣ የሴቶች ተሳትፎና የማብቃት ስትራቴጂዎች እንደዚሁም ከቡድን መሪ ጀምሮ በአመራር ደረጃ ለሚገኙ የመ/ቤቱ ሴት ሠራተኞች "Women in Leadership Position Challenges & Prospects" በሚሉ አርእስቶች ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡፣
- ሠራተኛው የዓመቱ የአለም የኤድስ ቀን መሪ ቃል "አንድም ሰው በኤች.አይ.ቪ. እንዳይያዝ ኃላፊነታችንን እንወጣ!!!" የሚል መሪ ቃልና የቀይ ሪቫን መልዕክት በደረት ላይ በማድረግ እርስ በእርስ እንዲወያዩ ተደርጓል፣
- የመ/ቤቱ ሰራተኛ የተሳተፈበት የ2003 የችግኝ ተከላ ፕሮግራም በኦሮሚያ ክልል ገላን ከተማና በድሬ ግድብ አከባቢ የተከናወነ ሲሆን በሶሻልና ኢንቫሮሜንት ኮሚቴ አማካይነት ለተተከለው ችግኝ ክትትል በመደረግ ላይ ነው፡፡

ለኦዲተሮችና የሂሳብ አዋቂዎች የሙያ ማረጋገጫ

መስጠትና መከታተልን በተመለከተ

118.በአዋጅ ቁጥር 669/2002 አንቀጽ 5/16 በተሰጠን ስልጣን መሠረት ከጥር 2003 እስከ ታህሣሥ 2004 ባለው ጊዜ ለ2 የግል ኦዲተሮችና ለ88 የግል ሂሣብ አዋቂዎች አዲስ የሙያ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠ ሲሆን ቀደም ሲል ፈቃድ በተሰጣቸው ኦዲተሮች ላይ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ አዲስ ደረጃ ምደባ ተደርጎላቸዋል፡፡

119.በሌላ በኩል የመንግሥት መ/ቤቶች እና የልማት ድርጅቶች በጠየቁት መሠረት በየደረጃው ለሚገኙ 13 ለሚሆኑ የውስጥ ኦዲተሮች የሙያ ደረጃ ማረጋገጫ ተሰጥቷል።

120.በደንብና መመሪያ መሠረት በ2004 በጀት ዓመት ለ69 የተፈቀደላቸው የግል ኦዲተሮች እና ለ324 የተፈቀደላቸው የሂሣብ አዋቂዎች የሙያ ብቃት የምስክር ወረቀት ታድሶ ዝርዝራቸውን ተጠቃሚዎች እንዲያውቁት ተደርጓል፡፡

የመ/ቤቱ የሰው ኃይል ሁኔታ

121.ለመ/ቤቱ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል ለኦዲት ባለሙያ 395 እና ለድጋፍ ሰጪ 215 በድምሩ 610 ሲሆን፤ ከጥር 2003 እስከ ታህሣሥ 2004 ድረስ 30 የኦዲት ባለሙያዎችና 7 የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በድምሩ 37 ሰራተኞች የተቀጠሩ ሲሆን፣ 2 የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በጡረታ የተገለሉና 30 ኦዲተሮችና 7 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በራሣቸው ፈቃድ በድምሩ 39 ሠራተኞች መ/ቤቱን ለቀዋል፡፡

122.በመሆኑም በኦዲት ዓመቱ መጨረሻ በመ/ቤቱ የነበሩ የኦዲት ባለሙያዎች 153 ወንዶችና 83 ሴቶች በድምሩ 236፤ የድጋፍ ሰጪ 69 ወንዶችና 69 ሴቶች በድምሩ 138 ሠራተኞች፤ በአጠቃላይ 374 ሠራተኞችና ኃላፊዎች በሥራ ላይ የነበሩ ሲሆን 236 የሥራ መደቦች በክፍትነት ተመዝግበው ይገኛሉ፡፡

የ2003 በጀት ዓመት የበጀት አጠቃቀም

123.በ2003 የበጀት ዓመት ለመ/ቤታችን የተፈቀደው በጀት ብር 16,346,966.26 ሲሆን፤ ሥራ ላይ የዋለው ብር 14,716,703.45 ወይም ከበጀቱ 90% ሆኗል፡፡

መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮች

124.መ/ቤታችን በሕገ መንግሥትና የማቋቋሚያ አዋጁ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ቢሆንም፤ በአንዳንድ ችግሮች ምክንያት ያሰበውን ያህል መራመድ አልቻለም፡፡ ካጋጠሙት ችግሮችም መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ኦዲቱን በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ለማከናወን የሚያስችል በቂ ክህሎትና ልምድ ያለው ባለሙያ ከደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ማነስ ጋር በተያያዘ መቅጠርና መያዝ አለመቻሉ፣
- ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ሂሣባቸውን በወቅቱ ዘግተው ለኦዲቱ አለማቅረብ፣ ስራ አመራር ሪፖርት ላይ በወቅቱ ምላሽ አለመስጠትና አንዳንድ የስራ ኃላፊዎች ለልዩልዩ ማብራሪያዎችና ጉዳዮች ሲፈለጉ በወቅቱ አለመገኘት፤

- ኦዲት ተደራጊዎች በሚሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች መሠረት በወቅቱና በተሟላ ሁኔታ የማስተካከያ እርምጃ አለመውሰድ፣

የ2004 በጀት ዓመት ሂሣብ የኦዲት ዕቅድ

125.በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት መሠረት የ2004 የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ሽፋኑን 100%፣ የክዋኔ ኦዲትን ደግሞ 36 ማድረስ የሚኖርብን ቢሆንም ለም/ቤቱ ቀርቦ ማሻሻያ የተደረገበት የመ/ቤቱ መዋቅር በህዳር 2004 ዘግይቶ በመመለሱና የታሰበው የሰው ኃይል ባለመሟላቱ የ2004 በጀት ዓመት ሂሣብ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲቱን ሽፋን 96.7%፣ የክዋኔ ኦዲትን ደግሞ በቁጥር 27 እና የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ተከታታይ ኦዲትን በቁጥር 270 ለማከናወን ታቅዶ የኦዲቱ ሥራ ከየካቲት 1 ቀን 2004 ጀምሮ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና

በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወነ ኦዲት

126.የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ በተሰጠው ኃላፊነት በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩ እና በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን፣ በመንግሥትና በውጭ ሀገር መንግሥታት ድጋፍ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን፣ እንዲሁም የዕርዳታ ሂሳቦችን ኦዲት እንደሚያደርግ ይታወቃል። ሆኖም ራሱ ከሚሰራው በተጨማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፣ ፕሮጀክቶችንና የዕርዳታ ሂሳቦችን በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና ከመ/ቤቱ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት በማስደረግ ላይ ይገኛል። በዚሁ መሠረት በኦዲት ድርጅቶቹ ኦዲት ተደርገው በሚቀርቡ ሪፖርቶች መነሻነት መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች አስፈላጊው ማሻሻያዎችና እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለኦዲት ተደራጊው ድርጅቶች፣ ለሥራ አመራር ቦርድና ለተቆጣጣሪ መ/ቤቶች በደብዳቤ አስፈላጊው ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

127.የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የ2003 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ እና በግል የኦዲት ድርጅቶች በተከናወኑ ኦዲቶች የታዩ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች በዋና ኦዲተር መ/ቤት ዘገባ ጥራዝ 2 ክፍል 3 በዝርዝር የቀረበ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ኦዲት የተደረጉ ድርጅቶች የሂሣብ መግለጫ ሁኔታ

128.በ2003 በጀት ዓመት ኦዲት የተደረጉት የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 99 ሲሆኑ፣ በኢትዮጵያ መንግሥትና በውጭ መንግሥታት የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ደግሞ 146 በድምሩ 245 ኦዲቶች ተከናውኗል፡፡

129.በእነዚህ ሪፖርቶች ላይ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት ዓይነት ሲተነተን፣ ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት 95፣ ነቀፌታ ያለበት አስተያየት 144፣ አቋም የማይወሰድበት አስተያየት 7 እና ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የቀረበበት 2 በድምሩ 245 ናቸው፡፡

130.በሌላም በኩል እስከ ሰኔ 30 ቀን 2003 መጨረሻ ባለው መረጃ መሠረት ከሁለት ዓመታት በላይ ሂሣባቸውን ዘግተው ኦዲት ያላስደረጉ 22 የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና መ/ቤቶች ይገኛሉ፡፡ ስለዚህ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት እነዚህ ድርጅቶች ሂሣባቸውን ዘግተው ኦዲት እንዲያስደርጉ በቅርበት ሊከታተሉት ይገባል፡፡

ኮርፖሬሽኑ ባካሄዳቸው ኦዲቶች የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች

131.ኮርፖሬሽኑ ባካሄዳቸው ኦዲቶች የታዩ አጠቃላይ ችግሮች በርካታ ሲሆኑ በተለየ ጥራዝ በቀረበው ዘገባ በዝርዝር የተጠቀሱ ቢሆንም ዋና ዋናዎቹ፤

- በርካታ ድርጅቶች የቋሚ ንብረት መቆጣጠሪያ ዝርዝር መዝገብ የሌላቸው፣ ያላቸውም ቢኖሩ ደግሞ ብዙዎቹ ምዝገባቸው ያልተሟላ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ የተለያዩ ቋሚ ንብረቶችን በአንድ ላይ መዝግበው የተገኙ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች በመጋዘን የሚገኙ ዕቃዎችን ቆጠራ የማያደርጉ ወይም በከፊል ቆጠራ የሚያደርጉ ሲሆን፤ ሌሎቹ ደግሞ ቆጠራ ቢያደርጉም ከሂሣብ መዝገብ ጋር የማይገናዘብ መሆኑ፣
- አብዛኞቹ ድርጅቶች በርካታ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ሂሳብ የተገኘባቸው ሲሆን ሂሳቡን ለመሰብሰብ ተገቢውን ጥረት ያላደረጉ ከመሆኑም በላይ አጠራጣሪ ለሆኑት ተሰብሳቢ ሂሣቦች በቂ መጠባበቂያ ያልያዙ መሆኑ፣

- በርከት ያሉ ድርጅቶች ለመንግሥት መክፈል የሚገባቸውን ከደመወዝ የተቀነሰ የሥራ ግብር፣ የጡረታ መዋጮ እንዲሁም የንግድ ትርፍ በወቅቱ የማይከፍሉ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ሂሳባቸውን በወቅቱ አለመዝጋታቸውና እንዲዘጉም የሚደረገው ግፊት የሚፈለገውን ያህል አለመሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ተከፋይ ብለው ከያዙት ሂሣብ ውስጥ ለረዥም ጊዜ ሣይከፈሉ የቆዩና ለማን መከፈል እንዳለባቸው የማይታወቁ ሂሣቦች መኖሩ፣

ናቸው፡፡

የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን

የሥራ እንቅስቃሴና ያጋጠሙ ችግሮች

የሥራ ክንውን

132.በ2003 በጀት ዓመት በነበረው 112 የሰው ኃይል 235 ኦዲቶችን ለማድረግ አቅዶ 252 ኦዲቶችን ወይም የዕቅዱ 107.23% ለመፈጸም ችሏል፡፡ ከ2002 በጀት ዓመት ክንውን ጋር ሲነፃፀር በ30 ሪፖርት ወይም በ14% ብልጫ አሳይቷል፡፡

133.ኮርፖሬሽኑ በ2002 በጀት ዓመት ከኦዲት ሥራ አገልግሎት ብር 9.94 ሚሊዮን ገቢ ለማግኘት አቅዶ ብር 11.55 ሚሊዮን ገቢ አግኝቷል፡፡ በሌላም በኩል ብር 7.48 ሚሊዮን ወጪ ለማድረግ አቅዶ ብር 7.81 ሚሊዮን ወጪ በማድረግ የብር 3.73 ሚሊዮን ትርፍ ሊያገኝ ችሏል፡፡

ማጠቃለያ

134.በሪፖርቱ እንደተመለከተው የ2003 በጀት ዓመት ሂሣብ የኦዲት ሽፋን 92.07% ደርሷል፡፡ ዓመታዊ የኦዲት ዕቅድ ክንውናችንም የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት 100% እና የክዋኔ ኦዲቱም ረገድ 17 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶችን ለማውጣት ታቅዶ 15ቱን በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ ሲጠናቀቁ 2 ደግሞ በ1 ወር ዘግይተው ወጪ ተደርጓል፡፡ በዳሰሳና ቅኝት ደረጃ የሚገኙ 5 ክዋኔ ኦዲቶችም በዕቅዱ መሰረት ወደ ቀጣዩ ዓመት የተላለፉ ስለሆነ፤ ውዝፍ የኦዲት ሥራ ባለመኖሩ ወቅታዊ የኦዲት መረጃን ማመንጨት ተችሏል፡፡ ይሁንና የኦዲት ጥራት ጉዳይ አሁንም ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ እንዳሚገባ እንገነዘባለን፡፡

135.በአጠቃላይ አሁን የተደረሰበት ውጤት የሀገራችን የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት እየተሻሻለ የመጣ መሆኑን የሚያመለክት ቢሆንም፤ ትኩረት ተሰጥቶ እርምጃ ባለመወሰዱ ብቻ በየዓመቱ በተደጋጋሚ የሚታዩት ዋና ዋና ግድፈቶች በአፋጣኝ ሊቀረፉ ይገባል፡፡ ዝርዝር የፋይናንሻልና የህጋዊናት ኦዲት ሪፖርት በሁለት ጥራዝ፤ እንደዚሁም ዝርዝር የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት በ17 ጥራዝ ተዘጋጅቶ ለአፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት የተላከ በመሆኑ፤ ም/ቤቱ በመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በኩል በጥልቀት መርምሮ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

136.በሌላ በኩል እርምጃ ሳይወሰድባቸው ከዓመት ወደ ዓመት የሚተላለፉ የተሰብሳቢ ሂሣቦች፣ ደንብና መመሪያን ሳይጠብቁ የሚፈጸሙ ግዥዎች፣ ከመንግሥት ገቢ አተማመንና አሰባሰብ ጋር ተያይዞ በየዓመቱ የሚታዩ ተመሳሳይ ችግሮች፣ ከውስጥ ገቢ አሰባሰብና ሪፖርት አደራረግ አንፃር የሚታዩ ችግሮች፤ የመንግሥት ንብረት አያያዝና አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ችግሮች፤ በኦዲት ሪፖርቶች የማሻሻያ አስተያየቶች መሠረት እርምጃ የማይወስዱ አካላትን በተመለከተ የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በመታገዝ ኦዲት ተደራጊዎች በጊዜ ገደብ የታጠረ የማስተካከያ መርሀ-ግብር ነድፈው እንዲያቀርቡ በማድረግ የክትትልና ቁጥጥር ፕግሮራም በመንደፍና የግድፈቶቹን መንስኤዎች በማጣራት ከሥረ መሠረቱ ለማስወገድ ሊሠራ ይገባል፡፡ እንደዚሁም በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት ቢያንስ ከ70-80% የሚሆኑት የፌዴራል

ባለበጀት መ/ቤቶች ነቀፌታ የሌለበት የኦዲት አስተያየት እንዲያገኙ የሚመለከታቸው አካላት በጋራ መርሀ-ግብር ነድፈው ሊሠሩ ይገባል፡፡

137.በመጨረሻም የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የቀረፃቸውን የአሠራር ማሻሻያዎችና ስትራቴጂዎችን በሚገባ በመተግበር ይበልጥ እንዲጠናከርና የምክር ቤቱን የክትትልና የቁጥጥር ተግባር በተሻለ ደረጃ እንዲያግዝ በተለይም ብቃት ያለው የሰው ሀይል እንዲያፈራ ከማስቻል አንጻር ሁሉን አቀፍ ድጋፍና ክትትል እንዲደረግለት እየጠየቅሁ በጥሞና ስላዳመጣችሁን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡